## ከ COVID-19 በተያያዙ ምልክቶች ህክምና እያገኙ ከሆነ የሚጠብቁት ነገር

Inova እንደ የዓለም የጤና ደርጅትና የበሽታ መከላከያና መቆጣጠርያ ማእከል የመሳሰሉ መሪ የጤና ድርጅቶች በሚያቀርቡት ምክረ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለ COVID-19 ታካሚዎች እንክብካቤ ያቀርባል፡፡ ዛሬ በሆስፒታላችን ውስጥ የሚያገኙት ነገር ከዚህ በፊት ከነበረው የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ምግቦ የሚቀርበው ተጠቅመው በሚጣሉ ሰሀኖችና እንዲሁም የሚወስዱትን የፈሳሽ መጠን ልንለካው እንችላለን፡፡ ስለ ቆይታዎ ተጨማሪ ልንነግሮት እንፈልጋለን፡፡

| ስለ ህክምና |
| --- |
| ከእንክብካቤ ቡድናችን (ሀኪም፣ ነርስ፣ የመተንፈሻ ተራፒስቶችና ቴክኒሻኖች) ጋር **በሌላ ቋንቋ መነጋገር የሚፈልጉ ከሆነ** ያለምንም ክፍያ በስልክ ወይ በቪድዮ አስተርጓሚ ለመጠቀም ደስተኛ ነን፡፡ የኛ ዓላማ በሆስፒታላችን ውስጥ በሚያገኙት የእንክብካቤ እቅድ እንዲረዱና ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡ |
| ከክፍሎ በተደጋጋሚ እንዳይወጡ ለማድረግ የእንክብካቤ ቡድኑ በአንድ ግዜ ብዙ ተግባራትን ይፈፅማሉ፡፡ በአካል ወደ ክፍሎ ሳንገባ በመስኮት ወይ በጥሪ በተን ልናናግሮት እንችላለን፡፡ ይህም የኢንፌክሽን ስጋትና የምንጠቀምባቸውን የጓንት፣ ጋውንንና የፊት ጭምብል መጠን ይቀንሳል፡፡ **የግል መከላከያ መሳርያ** በተጨማሪም PPE ተብሎ የሚጠራው የቫይረሱን መስፋፋት ለመቀነስ ያግዘናል፡፡ |
| **እንቅስቃሴ ማድረግ ለደም ፍሰት፣ የሳምባና ለጡንቻ አስፈላጊ ነው፡፡** አልጋ ላይ የሚተኙበት ወይ ክፍል ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን መመርያ እንሰጦታለን፡፡ የአተነፋፈስ እንቅስቃሴ መመርያ የምንሰጦት ሲሆን እነዚህን መመርያዎች በምን ያህል ግዜ እንደሚያደርጉት ያለውን መመርያ መከተል አስፈላጊ ነው፡፡ አስፈላጊ የሆኑ ምርመራዎችን ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር ከክፍሎ አይወጡም፡፡ ከክፍሎ ሲወጡ የሚያደርጉት የአፍ ጭምብል ይቀርብሎታል፡፡ |
| የ COVID-19 ምርመራ ውጤት ለማወቅ **24 ሰዓት ይወስዳል፡፡** |
| **ጥየቃ** |
| **የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ የጠያቂዎችን ቁጥር ቀንሰናል፡፡** በአንድ አንድ የተለየ ሁኔታ ብቻ ጠያቂዎች እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ ታካሚዎቻችን ከሚወዷቸው ጋር በስልክና በቪድዮ እንዲገናኙ እናበረታታለን፡፡ ከቤተሰብና ጓደኞች ጋር ለመገናኘት ድጋፍ ከፈለጉ ያሳውቁን - እኛ ድጋፍ እናደርግሎታለን፡፡ |
| Inova **በሆስፒታልና የማገገምያ ቆይታዎ ላይ ከቤተሰብና ጓደኞች ጋር ለመገናኘት የሚያስችሎትን** ነፃ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ **ድህረገ ገፅ** ለማቅረብ ከCaringBridge ተጣምሯል፡፡ ተጨማሪ ዝርዝር ለማግኘት ድህረ ገፃችንን ይጎብኙ፡ https://www.inova.org/patient-and-visitor-information/caringbridge |
| **እባክዎትን የግል ንብረቶን ይቀንሱ፡፡** በኢንፌክሽን ምክንያት ከቤት ምግብ ማምጣት አይቻልም፡፡ |

Inova በዚህ ወረርሽኝ ወቅት እርስዎን፣ ቤተሰቦንና ማህበረሰቡን ይደግፋል፡፡ የኛ ተልእኮ ሁልም ግዜ፣ በእያንዳንዱ ቦታና ለእያንዳንዱ ማህበረሰቡ ውስጥ ለሚኖረው ሰው ደረጃውን የጠበቀ የጤና እንክብካቤ ማቅረብ ነው፡፡

**ተጨማሪ መረጃ፡** https://inova.org/covid19